# ዕውቀቱን መዝረፍ...



ኣዳምና ሄዋን ከገነት ሲላፉ
ሰተት ብሎ ገብቶ ያ ባለወንጭፉ
ዕባቡን ሸሽገው ከዕጸ-በለስ ዛፉ...

ያ ባለወንጭፉ ባጠመደው ወጥመድ
ጨቅላውን የሰው ዘር ጭቃ፣ ትብያ፣ ኣመድ፣
ጠልፎ ጣለውና ኣሰረው በገመድ።



ያ ባለወንጭፉ ባመጣብን ጣጣ
ለውሉደ ኣዳም የጣለብን ዕጣ
መድኃኒዓለም ዕዳ ሊከፍልልን መጣ።



እርሱ ደራሲው፣ እርሱ ተዋናዩ
እስኪ ተመልከቱ፣ መላእክቶች እዩ
ፈጣሪን ከፍጡር በምኑ ትለዩ?

ምስጢረ ኅቡኣት ረቂቁ ምስጢሩ
ሓቁን ለመናገር ከችሎት ቢጠሩ
ሦስቱም ይቅረቡና እስቲ ይመስክሩ!



የትንኝ ጻድቃን፣ የትንኝ ሓጥኣን
ከትንኝስ ትንኝ፣ የትኛው ማንን
የቱ ሊጸድቅ ይሆን፣ የቱ ሊኮነን?

ፍጡራንን ፈጥሮ ያሰቃየውን
ይጠጣው ሓሞቱን ይቅመስ ፍዳውን!
ግረፉት፣ ስቀሉት፣ ይክፈል ዕዳውን



ፍጡራን ደካሞች ጥፋትም ቢያጠፉ
ዋና ወንጀለኛው ያን ባለወንጭፉ
ጐልጐታ ቀራንዮ መስቀል ላይ ለጥፉ።



ፍጡር ፈጣሪውን በኣምሳሉ ፈጥሮ
በጨርቅ ሸፍኖ፣ በመቅደስ ኣኑሮ
ያመልከው የለም ወይ ኣጥቁሮ/ኣሳምሮ?

ጠፈር ከዋክብቱን ፈጥሮ የቆጠረው
ሰማይን ያለ ዓምድ ኣቁሞ ያኖረው
ባለ ወንጭፉንስ ታድያ ማን ፈጠረው?





ፈጣሪውን ፈጥሮ ኋላም የሰቀለው
ተረት የገመደው፣ ታሪክም የቋጨው
ያ ባለወንጭፉም የሰው ሰው እኮ ነው...



ሰውና ፈጣሪ ነው ምን እና ምን?
ኣንዱ እያፈረሰ ሌላው ሲጠግን
ሰይጣን ፈጣሪ ነው፣ ሰውም ነው ሰይጣን።

ሰው፣ ሰይጣን፣ ፈጣሪ፣ እነዚህ ሠለስቱ
ምስጢረ ሥላሴ እንዲህ ሲከሰቱ
ፀጉር ስንጠቃውን እንዳትሳሳቱ!!!

ገ/ኢ. ጐርፉ።